# ለፕሪ ኬ እስከ 12 የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት የመቻል ደረጃ ገለጭ ቃለት

ለተጠቀሰው የእንግሊዝኛ ብቃት፣ **ከእገዛ ጋር**፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚከተሉትን ይችላሉ፤

| | ደረጃ 1<br>አዲስ ገቢ | ደረጃ 2<br>ጀማሪ | ደረጃ 3<br>በማደግ ላይ ያለ | ደረጃ 4<br>በመበልጸግ ላይ ያለ | ደረጃ 5<br>የቀረውን በማጠናቀቅ ላይ | ደረጃ 6 መድረሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| መስማት | • ወደ ተጠቀሱ ስዕሎች፣ ቃላት፣ ሐረጎች ይጠቁማል<br>• ባለ አንድ ደረጃ የአፍ አቅጣጫዎች ሲሰጡት ይከተላል<br>• አፋዊ ንግግሮችን ከቁሶች፣ ምስሎ ወይም ስዕሎች ጋር ያዛምዳል | • በተሰጠው የቃል መመሪያ መሰረት ስዕሎችን፣ ቁሶችን ለይቶ ይደረድራል<br>• ባለሁለት ደረጃ የቃል መመሪያን ይከተላል<br>• ከቃል ገለጻዎች በመነሳት ወደ ቁሳች፣ ስዕሎች መረጃን ያዛምዳል | • ከተሰጠው የቃል መመሪያ ላይ በመነሳት መረጃን ፈልጎ ያገኛል፣ ይመርጣል፣ በተራ ያስቀምጣል<br>• ባለብዙ ደረጃ የቃል መመሪያዎችን ይከተላል<br>• ስዕሎችን እና ቁሶችን በመጠቀም የቃል መረጃን ይመድባል ወይም በቅደም ተከተል ያስቀምጣል | • ከቃል መረጃ በመነሳት ተግባራትን፣ ዝምድናዎችን ያነጻጽራል/ያወዳድራል<br>• የቃል መረጃን በመተንተን ይተገብራል<br>• ከቃል አባባሎች በመነሳት መንስዔ እና ውጤቶችን ለይቶ ያውቃል | • ከቃል መረጃ ላይ በመነሳት ከድምዳሜ ላይ ይደርሳል<br>• በቃል ንግግር ላይ በመመርኮዝ ሞዴሎችን ይፈጥራል<br>• ከቃል ንግግር ግንኙነትን ይፈጥራል | |
| መናገር | • የቁሶችን፣ የሰዎችን የስዕሎችን ስም ይናገራል<br>• አምስቱ WH - (ማን፣ ምን፣ መቼ፣ የት፣ የትኛው) ጥያቄዎች ይመልሳል | • WH- ጥያቄዎች ይጠይቃል<br>• ስዕሎችን፣ ከስተቶችን፣ ቁሶችን፣ ሰዎችን ይገልጻል<br>• እውነታዎችን መልሶ ይናገራል | • መላምቶችን ያናገራል፣ ግምት ይሰጣል<br>• ሂደት፣ አሰራር ቅድምተከተሎችን ያብራራል<br>• ታሪኮችን ወይም ገጠመኞችን መልሶ ይተርካል | • ታሪኮችን፣ ጉዳዮችን፣ ጽንሰ ሃሳቦችን ያብራራል<br>• ንግግሮችን ያደርጋል፣ የቃል ሪፖርት ያቀርባል<br>• ለተግዳሮቶች፣ ችግሮች ፈጠራ የተሞላ መፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል | • በክርክር ላይ ይሳተፋል<br>• ክስተትን ያብራራል፣ ምሳሌዎች ይሰጣል እና መልሶችን ያስረዳል<br>• አስተሳሰብን ይገልጻል፣ ተከራክሮ ያሳምናል | |
| ማንበብ | • አዶዎችን ምልክቶችን ከቃላት፣ ከሐረጎች ወይም ከአካባቢ ተወስደው ከታተሙ ጋር ያዛምዳል<br>• ስለታተሙ እና የጽሁፍ ባህሪዎች ስላሉ ጽንሰ ሃሳቦች ለይቶ ያውቃል | • መረጃን ፈልጎ አግኝቶ በቦታው ይመድባል<br>• እውነታዎችን እና ግልጽ መልእክቶችን ለይቶ ያውቃል<br>• ከእውነታ ጋር የተያያዙ የቋንቋ ስርዓት ጥለቶችን ይመርጣል | • ስዕሎችን፣ ክስተቶችን፣ ሂደቶችን በቅደምተከተል ያስቀምጣል<br>• ዋንኛ ሃሳቦችን ለይቶ ያውቃል<br>• የቃልን ትርጉም ለማወቅ የቃል አገባብ ፍንጭን ይጠቀማል | • መረጃን ወይም ውሂብን/ዳታን/ ይተረጉማል<br>• ዋንኛ ሃሳቦችን የሚደግፉ ዝርዝሮችን ፈልጎ ያገኛል<br>• የቃል ቤተሰቦችን፣ ዘይቤያዊ አነጋገሮችን ለይቶ ያውቃል | • ከበርካታ ምንጮች መረጃን ለመሰብሰብ ጥናትና ምርምር ያደርጋል<br>• ግልጽ እና ስውር ከሆኑ ጽሁፎች ላይ በመነሳት ከድምዳሜ ላይ ይደርሳል | |
| መጻፍ | • ቁሶችን፣ ስዕሎችን፣ ዲያግራሞችን ስያሜ ይሰጣል<br>• ለቀረበለት ጥያቄ በስዕል መልስ ይሰጣል<br>• አዶዎችን፣ ምልክቶችን፣ ሐረጎችን መልእክት ለማስተላለፍ ይጠቀማል | • ዝርዝሮችን ይጽፋል<br>• ስዕሎችን፣ ሐረጎችን፣ አጫጭር ዓርፍተነገሮችን፣ ማስታወሻዎችን ይፈጥራል<br>• ከቃል ወይም ከጽሁፍ መመሪያ ለቀረበ ጥያቄ መረጃ ይሰጣል | • እንደወረደ ጽሁፎችን ወይም ተራኪ ጽሁፎችን ይጽፋል<br>• መረጃ ያነጻጽራል/ ያወዳድራል<br>• ክስተቶችን፣ ሰዎችን ሂደቶችን፣ የአፈጻጸም ቅደምተከተሎችን ይገልጻል | • ከግራፊክስ ወይም ማስታወሻዎች ማጠቃለያ ሃሳብ በጽሁፍ ያዘጋጃል<br>• ጽሁፍን አርትዕ ያደርጋል እና ያርማል<br>• ኦርጂናል ሃሳቦችን ወይም ዘርዘር ያሉ ምላሾችን ይጽፋል | • ወደ አዲስ ሁኔታዎች መረጃዎችን ይተገብራል<br>• ለተለያዩ ዘውጎች እና የጽሁፍ አቀራረቦች ምላሽ ይሰጣል<br>• በርካታ ዓይነት ቅርጾች፣ ዘውጎች ያላቸውን ጽሁፎች ይጽፋሉ | |

ይህን በመረጃ በመጠቀም ወቅት ተማሪዎች በሚኖራቸው ከውስጥ የጠለቀ እውቀት እድገት ሂደት ላይ በዕድሜ፣ በትምህርት ክፍል ደረጃ፣ ባላቸው የትምህርት ቤት ዓይነት ተሞክሮ እና (ተገቢነት ካለው) ተመርምረው በተደረሰባቸው የመማር ችሎታ ብቃት ማጣት ችግሮች የሚከሰቱ ልዩነቶች ከግምት ይገባሉ